የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

## የሰሜን አሜሪካ የኢሕአፓ አባላት ኮንፈረንስ ተካሄዶ በጥሩ ውጤት ተጠናቀቀ

ከ ሰኔ 24 እስከ ሰኔ 27 2003 (July 2-4) ባሉት ቀናት በዩናይትድ ስቴትስና በካናዳ ነዋሪ የሆኑ የኢሕአፓ አባላት በአሜሪካ አትላንታ ከተማ ውስጥ ስብሰባ አካሄደው ና በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይተው ግንዛቤዎችን ወስደዋል፤ አስፈላጊ ውሳኔዎችንም አስተላልፈዋል።

የኮንፈረንሱ ተሳታፊዎች በሀገራችን የፖለቲካ የሶሻልና የፖለቲካ ሁኔታ ላይ ውይይት አካሄደው ከሃያ ዓመት በፊት በመሳሪያ ኃይል ሥልጣን የጨበጠው ከፋፋዩና ዘረኛው የወያኔ ቡድን በሕዝባችን ላይ እየፈጸመ ያለው ግፍና በደል ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሰ መሄዱንና በዚህም የተነሳ የሕዝቡ ስቃይና መከራ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሊደርስ መቻሉን ተገንዝበዋል። የገቢው መጠን ወትሮም አነስተኛ የሆነው ሕዝባችን የምግቦችና የሌሎች ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች ዋጋዎች ከሚገባው በላይ እያሻቀቡ በመሄዱቸውና አንዳንድ ቁሳቁሶችም እስከናካቴው ከገበያ ላይ በመጥፋታቸው ህይወቱ በሞት አፋፍ ላይ እየደረሰ መምጣቱ፤ የጤና የትምህርትና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶች ጥራታቸውና ስርጭታቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየወረዱ መምጣቻቸው፤ የሥራ አጡ ቁጥር እየጨመረ መሆኑ፤ ድህነትና ረሃብ መስፋፋቱ፤ ወያኔ በሲቪልና በወታደራዊ ተቋሞች ውስጥ ነባር ሠራተኞችን እያስወጣ ከራሱ ዘርና ከሌሎችም መልምሎ ታማኝ በሚላቸው ካድሬዎች መተካቱ የአንድ ዘር የበላይነትን የተላበሰው የወያኔን አምባገነን አገዛዝ ለማጠናከር የሚወስደው ርምጃ መሆኑ ፤ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ሰፋፊ የእርሻ መሬቶችን ለውጭ ከበርቴዎች በገፍ በመሸጥ ወያኔ ከፍተኛ የሆነ የሀገሪቱን ሀብት እየዘረፈ መሆኑና ሕዝቡን መሬት አልባ በማድረግ አገሪቱን አዲስና ዘመናዊ ለሆነ የባዕድ ቅኝ አገዛዝ አሳልፎ መስጠቱ፤ ወያኔ የተለያዩ የንግድ የእርሻና አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶችን በመቆጣጠርም ሆነ እንደ አባይ ግድብ ለመሳሰሉ ፕሮጀክቶች በመዋጮ ስም ከደሃው ላይ በቀጥታ በመሰብሰብ መጠኑ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ እየዘረፈ መሆኑ፤ በቁጥጥር ስር ባደረጋቸው የአፈና ተቋሞች አማካይነት አሁንም በሕዝቡ ላይ የሚያካሂደው የአፈና ተግባራት በሰፊው መቀጠላቸው- በፓለቲካ አመለካከታቸውና እምነታቸው እንዲሁም የወያኔን የአፈና ተግባር በመቃወማቸው ብቻ የሚገድሉ፤ የሚታሠሩና በእስር ቤትም ሰቆቃዊ ድርጊት የሚፈጸምባቸው ዜጎች ቁጥር ከፍተኛ መሆኑ፤ ከወያኔ አፈና ለማምለጥና የስቃይን ኑሮ ለማስወገድ ወደ ጎረቤት አገሮች ወደ አረብና ምእራብ አገሮች በየጊዜው የሚሰደደው ኢትዮጵያዊ ቁጥር እጅግ ከፍተኛ መሆኑ፤ የራሳቸውን ጥቅም ብቻ የሚያሳድዱና የሚያምኑበትን መርህ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያዳግታቸው የምእራብ መንግሥታትና እንዲሁም ጥቅማቸውን የሚያስቀድሙ እንደቻይና ያሉ አገሮች ለወያኔ መንግሥት የሚቸሩት መጠኑ ከፍተኛ የሆኑ ብድርና እርዳታ አምባገነነትን እያጠናከረ መምጣቱ፤ አባላቱ ስብሰባ ከተወያየባቸውና ግንዛቤ ከወሰዱባቸው ጉዳዮች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ሕዝባችንን ከሚኖርበት የስቃይና የሲኦል ኑሮ ተላቆ ነጻነቱን አግኝቶና መብቱን አስከብሮ፣ በብልጽግና፣ በእኩልነት፣ በአንድነትና በሰላም የሚኖርበት ሁኔታ ለመፍጠር የወያኔን አምባገነን አገዛዝ ሁለገብ በሆነ ሕዝባዊ ትግል ማስወገድና ዴሞክራሲያዊ በሆነ የፓለቲካ ስርዓት መተካት አሁንም አማራጭ የሌለውና ወቅታዊ የሆነ አጣዳፊ ተግባር መሆኑን ኮንፈረንሱ ተገንዝቧል። ለዚህም ተደራጅቶ ግንባርን ሳያጥፉ፣ በጥቃቅን መሰናከሎች ሳይሸበሩና ተስፋ ሳይቆርጡ፣ መታገል ለአገርና ለወገን ፍቅር ያላቸው ወገኖች የወቅቱ ግዳጅና ኃላፊነት መሆኑን ኮንፈረንሱ አጢኗል። በሰሜን አፍሪካና በመካከለኛው ምስራቅ በሚገኙ አንዳንድ የአረብ አገሮች ውስጥ ባለፉት ወራት የተካሄዱት ሕዝባዊ አመጾች ለረዥም ጊዜ ተንሰራፍተው የነበሩትን አምባገነንና ጨቋኝ አገዛዞች ያስወገዱ፤ አንዳንዶችንም እያንገዳገዱ ያሉ መሆናቸውን ስብሰባው ግንዛቤ ወስዶበት በእኛም አገር ተመሳሳይ ሁኔታ ሊመጣ የሚችልበትን ሁኔታ አጢኗል።


EPRP
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A
Tel. : (202) 291-4217
Fax : (202) 291-7645

EPRP
BP 22
Bois Colombes 92270
France

E-mail ESPIC@aol.com Website: http://www.EPRP.com

ከተመሠረተ ጀምሮ ላፍታም እንኳ ከትግል መድረክ ያልተለየውንና የጠላትና የተቀናቃኝ ድርጅቶችን ጥቃት ተቋቁሞ፤ የውስጥ እንቅፋቶችን አስወግዶ፤ ህልውናውን ጠብቆ በሕዝብ ውስጥ ከሕዝብ ጋር ሆኖ ከፍተኛ መስዋእትነት በመክፈል የሕዝብ አለኝታነቱን ያስመሰከረው ኢሕአፓ እያካሄደ ያለውን እንቅስቃሴ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ ኮንፈረንሱ መርምሯል። ባለፉት አመታት ሕዝባዊ ትግሉን ለማጠናከር ኢሕአፓ በሁሉም መስክ ላደረገው እንቅስቃሴ ስብሰባው አድናቆቱን ገልጿል። በተለይ በሀገር ውስጥ የሚገኙት የኢሕአፓ አካላትና አባላት ባላፈው ዓመት የጠላትን የጸጥታና የአፈና መዋቅሮች ተቋቁመው የፓርቲውን አርማ የያዙ ሕዝብን ለትግል የሚያነሳሱ ቀስቃሽ መፈክሮችን በየቦታው በመለጠፍና የተለያዩ መልአክቶችን ያዘሉ በራሪ ጽሁፎችን በመበተን ያደረጉት እንቅስቃሴ የሕዝቡን ተስፋ ከማለምለሙና የትግል መንፈሱን ከማደሱ በላይ የጠላትን ሠፈር አደናግጧል። በሰሜን አሜሪካ የሚኖሩ የኢሕአፓ አባላት በአገር ውስጥ ያሉ የኢሕአፓ አባላት መስዋእትነት በመክፈል እያደረጉ ያሉትን ትግል በከፍተኛ ደረጃ አድንቀው ይህንን ትግል ለማጠናከር በተለይ አስፈላጊውን ርዳታና ትብብር ለማድረግ ዝግጁነታቸውን አረጋግጠዋል። በጎረቤት አገራት፤ በአሺያኒያ፤በአውሮፓ፤ በሰሜን አሜሪካና እንዲሁም በተለያዩ አገሮች ያሉ የኢሕአፓ አባላት ሕዝባዊ ትግሉን ለማጠናከር እያደረጉ ያሉትን እንቅስቃሴ ኮንፈረንሱ አድንቆ ይህንን ይበልጥ ለማጠናከር አስፈላጊ ርምጃዎች እንዲወሰዱ ለፓርቲው አመራር ማሳሰቢያ አስተላልፏል።

የወደፊቷ ኢትዮጵያ የወጣቱ ትውልድ እጣ ፋንታ በመሆኑ ወጣቱ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት፤ ለአገር አንድነትና ሉዓላዊነት በሚደረገው ትግል ውስጥ ተሳታፊ መሆኑ ወሳኝነት ይኖረዋል። ድርጅታችን ኢሕአፓ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ወጣቶች ክንፍ ድርጅት (ኢወክንድ) እንዲሚሰረት ማድረጉን ኮንፈረንሱ አድንቆ ኢወክንድ ትግሉን ለማጠናከር በሚያደርገው እንቅስቃሴ ሁሉ ሙሉ ትብብር ለማድረግ የስብሰባው ተሳታፊዎች ዝግጁነታቸውን ገልጸዋል።

ሴቶች እህቶቻችን በዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት አማካይነት ተሰባስበው በተለያዩ መንገዶች በሴቶች ላይ የሚደርሱትን በደሎች ለመቃወምና ለማስወገድ እንዲሁም የሴቶችን ነጻነትና መብት ለማስጠበቅ የሚያደርጉትን ትግልና እንቅስቃሴ ኮንፈረንሱ አድንቆ በሚያስፈልገው ሁሉ ከጎናቸው ለመቆም ወስኗል። የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ) መብታቸው ለታፈነና በእስርና በሌላም መስክ ለሚሰቃዩ ኢትዮጵያውያን ጠበቃ በመሆን ለሚያደርገው ተጋድሎ ሁሉ ኮንፈረንሱ አድናቆቱን ገልጿል። ድርጅታችን ሕዝባዊ ትግል ለማጠናከር ባለፉት አመታት ያደረጋቸውን የኅብረት ጥረቶች ኮንፈረንሱ ገምግሞ ምንም እንኳ ችግሮችና ድክመቶች ቢኖሩም አሁንም የኅብረት ትግል አስፈላጊ መሆኑን አምኗል። ትግሉን ፍሬያማ ለማድረግ በሀገር ውስጥ ትግል የሚያካሄዱ ድርጅቶች በተግባር በተጨባጭ ትብብር እናድርግ በሚል ድርጅታችን በተደጋጋሚ ያደረገውን ጥሪ አስመልክቶ ኮንፈረንሱ ድጋፉን ሰጥቷል። በአገር ውስጥ መደረግ ያለበትን የትብብር ትግል ተግባራዊ ለማድረግ ሁሉም ኃይሎች የየበኩላቸውን ጥረት እንዲያደርጉ ጥሪውን አስተላልፏል።

ላለፉት 20 ዓመታት በሥልጣን ኮርቻ ላይ ተቀምጦ ሕዝባችንን በማሰቃየት ላይ የሚገኘውን ዘረኛ አምባገነንና ከፋፋይ ኃይል በሁለ ገብ ትግል አስወግዶ የሕዝብን መብት ያረጋገጠ፤ የአገሪቷን አንድነትና ሉዓላዊነት ያስጠበቀ፤ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን ለማደርግ ድርጅትን ማጠናከር አስፈላጊ መሆኑ ኮንፈረንሱ አስረግጦ ወጣቶች፤ አገር ወዳድ ታጋይ ኃይሎች፤ የቀድሞ አባላትና ሌሎች ኢሕአፓን ተቀላቅለው ትግሉን እንዲያጠናክሩ ጥሪውን አስተላልፏል።

አምባገነን አገዛዝ በሕዝባዊ ትግል ይወገዳል!!!
የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቸንፋል

ሰኔ 27 ቀን 2003 ዓ.ም.